# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ -ጾታ ጉዳይ እቅድና ፕሮግራሞች መካተታቸውንና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ በሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እና በፍትህ ሚኒስቴር ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

**ጳጉሜ 2007 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**

# ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ራዕይ፣ ተልዕኮ ........ 2

የፍትህ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር ........ 3

የሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር አደረጃጀትና የሰው ኃይል ........ 4

የሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የፋይናንስ ምንጭ ........ 4

የኦዲቱ ዓላማ ........ 4

ለከዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ ........ 5

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርት ........ 5

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 5

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት ........ 6

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 6

የሴቶችን ጉዳይ ማካተት ድጋፍና ክትትል ተግባር የአሰራር ስርዓት መግለጫ (SYSTEM DESCRIPTION) ........ 6

የሴቶችን ጉዳይ ማካተት ድጋፍና ክትትል ተግባር የአሰራር ስርዓት ሥዕላዊ መግለጫ (SYSTEM DESCRIPTION) ........ 8

ክፍል ሁለት ........ 9

የኦዲት ግኝቶች ........ 9

2.1 የስርዓት-ጾታ ጉዳይ በፍትህ ሚኒስቴር በሚዘጋጅ እቅድና ፕሮግራም ውስጥ መካተቱን፣ ለአፈፃፀምና ክትትል የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ........ 9

2.1.1 የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርን በተመለከተ፣ ........ 9

የስርዓት-ጾታን በሚመለከት በተዘጋጁት መመሪያዎች ላይ ስልጠና ስለመሰጠቱና መመሪያዎቹን ስለማሰራጨቱ፣ ........ 9

የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ በፍትህ ሚኒስቴር እቅድና ፕሮግራሞች ተካቶ ተግባራዊ እየተደረገ ስለመሆኑ የመስክ ክትትል ስለማድረጉ፣ ........ 10

የሴቶችን ጥቃት የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የአገሪቱ ሕግ አካል ሆነው እንዲፀድቁ መደረጉን በተመለከተ፣ ........ 11

የፍትህ ሚኒስቴር የስርዓት-ጾታ ኦዲት እንዲያካሂድ ያደረገውን ክትትል በተመለከተ፣ ........ 12

2.1.2 የፍትህ ሚኒስቴርን በተመለከተ፣ ........ 13

ፍትህ ሚኒስቴር ያለውን አደረጃጀት በተመለከተ፣ ........ 13

የፍትህ ሚኒስቴር የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ አመታዊ እቅድ ውስጥ አካቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣ ........ 14

የስርዓት-ጾታ ጉዳይ በፍትህ ሚኒስቴር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተታቸውን በተመለከተ፣ ........ 14

በፍትህ ሚኒስቴር የሚከናወኑ ተግባራት /አመላካቾች በጾታና በእድሜ የተለዩ መሆናቸውን በተመለከተ.................. 15
በፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ባሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በተመለከተ፣ ......................................... 16
የሴቶችን መብት በማስጠበቅ ረገድ ቸልተኛ የሆኑ የሕግ አስፈፃሚዎች ተጠያቂ የሚሆኑበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ........................................................................................ 17
የፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ማካሄዱን በተመለከተ፣ .................................................................. 18
በሴቶች ላይ ስለሚፈፀሙ ጥቃቶች ጥናት መደረጉን በተመለከተ፣ ............................................................... 18
2.2. የሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከፍትህ ሚኒስቴር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ከፍትህ ጋር በተያያዘ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ተካቶ ተግባራዊ ለማድረግ በቅንጅት የሚሰሩበት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲሁም መደበኛ የመወያያ መድረክ የዘረጉና ተግባራዊ ያደረጉ መሆኑን በተመለከተ፣.................................................. 19
በሴቶች ዙሪያ በሚወጡ ሕጎች ላይ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ መሰጠቱን በተመለከተ፣ ............................................. 19
ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች የሚደረግላቸውን ድጋፍና እገዛ በተመለከተ፣......................................................... 20
ክፍል ሶስት ........................................................................................................................ 22
መደምደሚያ ....................................................................................................................... 22
ክፍል አራት......................................................................................................................... 24
የማሻሻያ ሃሳቦች.................................................................................................................... 24
አባሪ 1፡ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር መዋቅር ....................................................................... I
አባሪ 2: የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች....................................................................................... II
አባሪ 3: በናሙና የታዩ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎችና የፍትህ ቢሮዎች ..................................................V

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. በብሔራዊ የህዝብና ቤቶች ቆጠራ (የ2004 የማእከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ትንበያ) መረጃ መሰረት የኢትዮጵያ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት 84,320,987 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ወንድ 42,556,999 ሴት 41,763,988 ነው፡፡ ምንም እንኳን ሴቶች የአገሪቱን ህዝብ ቁጥር ግማሽ ያህሉን የሚይዙ ቢሆንም ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር በማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ተሳትፎና ተጠቃሚነት ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሆኑም በአገሪቱ ውስጥ የሚካሄድ ህዝብን የሚመለከት ማናቸውም እንቅስቃሴ ሴቶችን ግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ እውነታ ሲታይ ህብረተሰባችን ለነዚህ አካላት ተገቢውን ትኩረት መስጠት እንዳለበት ያመለክታል፡፡

2. የሴቶች፣ ህጻናትና የወጣቶች እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት መብት ከአጠቃላይ በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚካሄድ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ተለይቶ የሚታይ ባይሆንም፣ በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ የተለየ ትኩረት ማግኘት የሚገባው ጉዳይ እንደሆነ አከራካሪ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሴቶች፣ ህጻናትና የወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በአገር አቀፍ ደረጃ ሴቶችን፣ ህጻናትንና ወጣቶችን አስመልክተው የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን የማስተባበርና አፈጻጸሙን የመከታተል ኃላፊነት አለበት፡፡

3. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የሴቶች ጥያቄ የሰብዓዊ መብት ጥያቄ መሆኑን በመገንዘብ በአለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ስምምነቶች፣ ሴቶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎችና ደንቦችን ለማስፈፀም በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የሴቶች ጉዳይ ንዑስ ዘርፍ በ1984 ዓ.ም እንዲቋቋም ተደርጎ በጥናት፣ በስልጠና፣ በውጭ ግንኙነትና በማህበራዊ ጉዳዩች ላይ ትኩረት አድርጎ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡

4. ከዚህም በተጨማሪ በሴቶች ላይ የሚታዩት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ መድሎዎች እንዲወገዱ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን በማስተባበር የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት በማሳደግ የሴቶች ደህንነት እንዲጠበቅ የማድረግ ተልዕኮ ነበረው፡፡

5. በመቀጠልም በ1984 ዓ.ም የመዋቅር ለውጥ ተደርጎ የወጣቶችን ጉዳይ በማካተት የሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ድርጅት በመባል እስከ 1989 ዓ.ም ሲሰራ ከቆየ በኂላ፣ ከነሀሴ 1989 ዓ.ም ጀምሮ የሕፃናት፣ ወጣቶችና ቤተሰብ ጉዳይ መምሪያ ተብሎ ወደ ሰራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲጠቃለል ተደርጎ ነበር፡፡

6. ስለሆነም መንግስት የሴቶችንና የሕፃናት ጉዳይ ልዩ ትኩረት እንደሚያስፈልገው በመረዳቱ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤትና በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበሩትን ሴቶችንና ሕፃናትን የተመለከቱ ኃላፊነቶችንና ተግባራትን በማዋሀድ በአዋጅ ቁጥር 471/98 የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲደራጅ ተደረገ፡፡

7. በመቀጠልም የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በመባል እንዲቋቋም ከመደረጉም በተጨማሪ በዚሁ አዋጅ የሚኒስትሮች የወል ስልጣንና ተግባር አንቀፅ 10 ተራ ቁጥር 4 "እያንዳንዱ ሚኒስቴር የሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና የወጣቶችን ጉዳይ እንዲያካትቱ መደረጋቸውን ማረጋገጥ" እንደሚኖርበት የተቀመጠ በመሆኑ እንዲሁም ለፍትህ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣንና ተግባር አንቀጽ 16 ተራ ቁጥር 11 "በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍትሐ ብሔር ክስ ለመመሥረት አቅም የሌላቸውን ዜጎች በተለይም ሴቶችንና ሕፃናትን ወክሎ ይከራከራል" በሚል ተገልጿል፡፡

## የሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ራዕይ፣ ተልዕኮ

<u>**ራዕይ**</u> (Vision)

8. የሴቶችና ወጣቶች በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊና በባህላዊ መስኮች እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት የተረጋገጠ የህጻናት መብትና ደህንነት የተከበረባትና የሥርዐተ-ጾታ እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ማየት፡፡

<u>**ተልዕኮ (Mission)**</u>

9. የሴቶችና የወጣቶችን እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነትን በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ማረጋገጥ፣ የሥርዐተ-ጾታ እኩልነትን ማስፈንና የህጻናትን መብትና ደህንነትን ማስጠበቅ፡፡

<u>**ሥልጣንና ተግባር**</u>

10. የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት የሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡ እነዚህም፡-

- ✓ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች መብትና ጥቅሞችን በማስከበር ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፤

- ✓ የሴቶችን፣ የሕፃናትና የወጣቶችን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል፤
- ✓ ሴቶችና ወጣቶች በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤
- ✓ ሴቶችና ወጣቶች እንደፍላጎቶቻቸውና እንደ ችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- ✓ በፌዴራል መንግስት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና የወጣቶችን ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤
- ✓ በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችን በጥናት በመለየት መድሎዎቹ የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
- ✓ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
- ✓ ሴቶች በተለያዩ የመንግሥት አካላት በውሳኔ ሰጪ የሥራ ቦታዎች ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤
- ✓ የሕፃናት መብትና ደህንነት እንዲጠበቅ የሚመለከታቸው አካላትን ያስተባብራል፤
- ✓ ሴቶችንና ሕፃናትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ውሎችን አፈጻጸም ይከታተላል፤ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፣

የሚሉ ናቸው፡፡

## የፍትህ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር

- የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 የሚኒስትሮች የወል ስልጣንና ተግባር አንቀፅ 10 ተራ ቁጥር 4 "እያንዳንዱ ሚኒስቴር የሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና የወጣቶችን ጉዳይ እንዲያካትቱ መደረጋቸውን ማረጋገጥ" እንደሚኖርበት
- ለፍትህ ሚ/ር በተሰጠው ስልጣንና ተግባር አንቀጽ 16 ተራ ቁጥር 11 "በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍትሐ ብሔር ክስ ለመመሥረት አቅም የሌላቸውን ዜጎች በተለይም ሴቶችንና ሕፃናትን ወክሎ ይከራከራል"

የሚል ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## የሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር  አደረጃጀትና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

11. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመራው በተቋሙ የበላይ አመራር አካል በሆኑ በአንድ ሚኒስትር ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡ ለሚኒስትሯ ተጠሪ የሆኑ 2 ሚኒስቴር ዴኤታዎች የሚገኙ ሲሆን በነርሱም ስር 11 ዳይሬክቶሬቶች ይገኛሉ፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ  ድርጅታዊ መዋቅር ሥዕላዊ መግለጫ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

12. የሚኒስቴር መ/ቤቱ እስከ መጋቢት ወር 2007 ዓ.ም ድረስ 117 (52%) ሴት ሰራተኞች 106 (47%) ወንድ ሰራተኞች በድምሩ 223 ቋሚ ሰራተኞች ያሉት ሲሆን፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለው የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን ማስተርስ (ሁለተኛ ዲግሪ) 9 (4%)፣ ቢ.ኤ ዲግሪ 97 (43%)፣ ዲፕሎማ 34(15%) ሰርተፊኬትና እና ከዛ በታች ያሉ 69 (31%) ናቸው፡፡

## የሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የፋይናንስ ምንጭ

13. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት  በሚመደብለት መደበኛ በጀት እና ከተለያዩ ድርጅቶች ከሚገኘው ዕርዳታ ከ2004-2007 ግማሽ ዓመት  ድረስ ከመንግስት የተመደበለት እና ከዕርዳታ ያገኘው ገቢና ሥራ ላይ የዋለው በጀት ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ላይ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | ከመደበኛ በጀት | | | ከዕርዳታ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተፈቀደ | ስራ ላይ የዋለ | ሥራ ላይ የዋለው በ% | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ | ሥራ ላይ የዋለው በ% |
| 2004 | 18,105,200.00 | 16,450,749.00 | 91%) | 49,980,367.00 | 35,206,627.40 | 70% |
| 2005 | 21,287,200.00 | 20,111,763.00 | 95%) | 41,534,985.66 | 36,849,507.00 | 87% |
| 2006 | 34,757,716.00 | 31,433,228.00 | 90%) | 40,511,633.00 | 32,520,534.00 | 80% |
| 2007 8ወር | 74,150,116.00 | 67,995,740.00 | 92% | 132,026,985.66 | 104,576,668.40 | 79% |

### <u>የኦዲቱ ዓላማ</u>

14. በተመረጠው የኦዲት አካባቢ እና የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ የክዋኔ ኦዲት ቢከናወን የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይን በፍትህ ሚኒስቴር እቅድና ፕሮግራሞች ውስጥ በማካተት እየተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ በሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ በፍትህ ሚኒስቴር እና

በባለድርሻ አካላት መካከል ያለው ቅንጅታዊ አሰራር እና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ላይ ያሉትን ችግሮች በመለየት የማሻሻያ ሃሳብ ለመስጠት ያስችላል፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ

15. "የስርዓተ -ጾታ ጉዳይ በፍትህ ሚኒስቴር እቅድና ፕሮግራሞች ውስጥ መካተቱን አፈፃፀምና ክትትሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ"

የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርት

### የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

16. ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተለዩ ሲሆን በመጀመሪያው የትኩረት አቅጣጫ ሥር ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ በፍትህ ሚኒስቴር በሚዘጋጁ እቅድና ፕሮግራም ውስጥ መካተቱን፣ ለአፈፃፀምና ክትትል የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፡፡
    1.1 የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ ስለማካተቱ በየበጀት ዓመቱ ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣
    1.2 የፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታ ማካተት የእቅድ አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣
2. የሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በየደረጃው ካሉ የፍትህ አካላት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ከፍትህ ጋር በተያያዘ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ተካቶ ተግባራዊ ለማድረግ በቅንጅት የሚሰሩበት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲሁም መደበኛ የመወያያ መድረክ የዘረጉና ተግባራዊ ያደረጉ መሆኑን መገምገም፤

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት

17. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን እና ሁለት የኦዲት ንዑስ ትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 29 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል። የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የአምስት ዓመት ውጤት ተኮር ዕቅድ፣ ብሔራዊ የሥርዓተ-ጾታ ማካተቻ ጋይድላይን፣ የፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታ ማካተቻ ጋይድላይን፣ የብሔራዊ አስተባባሪ አካል ስትራቴጂክ እቅድ፣ የፍትህ ሚኒስቴር ዕቅድ፣ በተባበሩት መንግስታት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ማናቸውንም አድሎ ለማስወገድ የወጣ ስምምነት፣ ብሔራዊ የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ማንዋል እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው። የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ


18. ኦዲቱ የሸፈነው ከ2004 እስከ 2007 የመጀመሪያው ሩብ በጀት አመት ያለውን ሶስት አመት ከሶስት ወራት ሲሆን በዋናነት የተከናወነው በሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እና በፍትህ ሚኒስቴር ሲሆን በተጨማሪም ከሚኒስቴር መ/ቤቶቹ ጋር በቅርበት ከሚሰሩ በናሙና ከተመረጡ ሶስት ክልሎች (ድሬዳዋ መስተዳድር፣ ሐረሪ እና ደ/ብ/ብ/ሕ/ ክልሎች) በሚገኙ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎች እና የፍትህ ቢሮዎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ እና ፍትህ ቢሮ እና በፍትህ ሚኒስቴር ስር በሆኑ በናሙና በተመረጡ የአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ አራት ክፍለ ከተሞች (በኮልፌ ቀራንዮ፣ ልደታ፣ ቂርቆስና ንፋስ ስልክ ላፍቶ) የፍትህ ጽ/ቤቶች በአካል ተገኝቶ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና ማስረጃዎችን ጠይቆ በመከለስ ነው። በኦዲቱ ወቅት የታዩ መ/ቤቶች ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል።

## የሴቶችን ጉዳይ ማካተት ድጋፍና ክትትል ተግባር የአሰራር ስርዓት መግለጫ (System description)

19. የሴቶችን ጉዳይ ማካተት ድጋፍና ክትትል ተግባር የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት በሁሉም የልማት መስኮች ለማካተት የሚመለከታቸውን አካላት የማስተባበር፣ የመደገፍና የመከታተል ሚና አንዱና ዋነኛው ሲሆን የሴቶችን ጉዳይ ተቋማዊነት ለማጎልበት ከፌዴራልና ከክልል ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ መዋቅሮች ለተውጣጡ ባለሙያዎች የመፈጸምና የማስፈፀም አቅምን ለማሳደግ እንዲቻል በስርዓተ-ጾታ ፅንሰ-ሃሳብ፣ ማካተት፣ ትንተና፣ ኦዲት እና በሥርዓተ-ጾታ ክትትልና ግምገማ ርዕሶች ላይ

የአሰልጣኞች ስልጠና በማዘጋጀትና በመስጠት የእውቀትና ክህሎት ክፍተቶችን ለመሙላት የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ የክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ የማካሄድ የሥራ ፍሰት ስዕላዊ መግለጫው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## የሴቶችን ጉዳይ ማካተት ድጋፍና ክትትል ተግባር የአሰራር ስርዓት ሥዕላዊ መግለጫ (System description)



# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## 2.1 የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ በፍትህ ሚኒስቴር በሚዘጋጅ እቅድና ፕሮግራም ውስጥ መካተቱን፣ ለአፈፃፀምና ክትትል የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣

### 2.1.1 የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርን በተመለከተ፣

***የስርዓተ-ጾታን በሚመለከት በተዘጋጁት መመሪያዎች ላይ ስልጠና ስለመሰጠቱና መመሪያዎቹን ስለማሰራጨቱ፣***

19. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታን በሚመለከት ባዘጋጃቸው መመሪያዎች (ብሔራዊ የስርዓተ-ጾታ ማካተቻ ጋይድላይን፣ የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ማንዋል....) ላይ ለፍትህ ሚኒስቴር፣ ለክልል የሴቶች ጉዳይና የፍትህ ቢሮዎች ስልጠና ሊሰጥ፣ ሊያሰራጭ፣ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊከታተልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
20. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በናሙና በታዩ ማለትም ለፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ላሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች (ኮልፌ ቀራንዮ፣ ቂርቆስ፣ ልደታና ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተሞች) እንዲሁም ለአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳደር፣ ለኦሮሚያ፣ ለሐረሪ፣ ለደቡብ /ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ክልሎች እና ለሲዳማ ዞን ፍትህ ጽ/ቤት ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎች እና ፍትህ ቢሮዎች የስርዓተ-ጾታን በሚመለከት ያዘጋጃቸውን መመሪያዎች ስለማሰራጨቱና በመመሪያዎቹም ዙሪያ ስልጠና ስለመስጠቱ በኦዲቱ ወቅት ማስረጃው እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡
21. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ለፍትህ ሚኒስቴር፣ ለሀረሪና ኦሮሚያ ክልሎች፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር ብሄራዊ የስርዓተ-ጾታ ማካተቻ እና የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ማንዋል ላይ ለተጠቀሱት ክልሎች የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ እንዲደርሳቸው የተደረገ መሆኑን በተዘጋጁት ማንዋሎች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እና የአሰልጣኞች ስልጠና በክልሎች ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮና ለፌዴራል ሴክተር መ/ቤቶች የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት መስጠቱን ቢገልፁም የኦዲት ሪፖርቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃው አልቀረበም፡፡

22. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስለሁኔታው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጠው አስተያየት የተዘጋጁት መመሪያዎች የተሰራጩና ስልጠና የተሰጠ መሆኑን ቢገልጽም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በአካል በመገኘት በታዩት ከላይ በተገለጹት የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎች መመሪያዎቹ እንዳልደረሳቸው የገለጹ ሲሆን በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በኩል መመሪያዎቹ ለተጠቀሱት ክልሎች ስለመላካቸው እና ስልጠና ስለመሰጠቱ የሚገልጹ ማስረጃዎች የኦዲት ሪፖርቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ሊቀርብ ባለመቻሉ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

23. በስርዓተ-ጾታ ዙሪያ የሚዘጋጁ መመሪያዎች ለክልል የሴቶች ጉዳይና የፍትህ ቢሮዎች ተሰራጭተው በመመሪያው (ማንዋሉ) ላይ ሥልጠና እንዲወስዱ ካልተደረገ የተዘጋጁት መመሪያ እና ማንዋሎች ተግባራዊ እንዳይሆኑ ክፍተት ሊፈጥር፣ እንዲሁም በስርዓተ-ጾታ ዙሪያ የሚከናወኑ ተግባራት በአግባቡ እንዳያከናውኑ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

**የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ በፍትህ ሚኒስቴር እቅድና ፕሮግራሞች ተካቶ ተግባራዊ እየተደረገ ስለመሆኑ የመስክ ክትትል ስለማድረጉ፣**

24. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በፍትህ ሚኒስቴር የሴቶችን ጉዳይ ማካተት ዙሪያ የሚያደርገውን የመስክ ክትትል በዓመታዊ እቅድ በመያዝ አፈጻጸሙን ሊከታተል፣ በመስክ ክትትል ወቅት በታዩ ችግሮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ክትትል ሊያደርግና ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

25. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የፍትህ ሚኒስቴር የሴቶችን ጉዳይ በማካተት ዙሪያ ያለበትን ደረጃ ለመገንዘብ በየሩብ ዓመቱ የሚገናኝበት መድረክ የዘረጋ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ ከ2004-2007 ግማሽ ዓመት ድረስ በመ/ቤቱ የመስክ ክትትል በማድረግ ሥርዓተ-ጾታን አስመልክቶ የተከሰቱ ችግሮች፣ ክፍተቶችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ለፍትህ ሚኒስቴር ስለማቅረቡ፣ በቀረበው ሪፖርት መሰረት ግብረ-መልስ ስለመስጠቱ እና በግብረ-መልሱ መሰረት እርምጃ እየተወሰደ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

26. በተጨማሪም በ2004 ዓ.ም እቅድ አፈፃፀም ላይ የስርዓተ-ጾታ ጉዳዮች በአግባቡ መካተታቸውን ለማወቅ የሚረዳ ቼክሊስት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ፍትህ ሚኒስቴርን ጨምሮ ለ21 የፌዴራል ሴክተር መ/ቤቶች ለአስተያየት መላኩ ታውቋል፡፡ ነገር ግን የሴክተር መ/ቤቶች አስተያየታቸውን ስለመላካቸው፣ በተሰጡት አስተያየቶች መሰረት ቼክ ሊስቱን ተስተካክሎና ጸድቆ ለሴክተር መ/ቤቶች በመላክ ቼክ ሊስቱ ተግባራዊ መደረጉን ቢገለፅም ቼክሊስቱ በ2004 በጀት ዓመት ሆነ በቀጣዮቹ በጀት

ዓመታት ጸድቆ ተግባራዊ ስለመደረጉ ማስረጃው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ እንዲቀርብ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

27. የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ በማካተትና የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን በማጎልበት አሰራር ላይ ሙያዊ ድጋፍ እና በመስክ ክትትል ሪፖርት ግብረ-መልስ የመስጠት ስራ ፍትህ ሚኒስቴርን ጨምሮ በ15 የፌዴራል ሴክተር መ/ቤቶች እንደተሰራ በ2005 ዓ.ም እቅድ አፈፃፀም ላይ የተገለጸ ቢሆንም በፍትህ ሚኒስቴር ላይ የተከናወነው የመስክ ክትትል ሪፖርት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልቀረበ መሆኑ፣ በ2006 እና በ2007 ግማሽ ዓመት ድረስ የመስክ ክትትል ስለመደረጉ በእቅድ አፈፃፀሙ ላይ አለመቀመጡ ታውቋል፡፡

28. ስለሁኔታው የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት የፍትህ ሚኒስቴር በ2005 የመስክ ክትትል ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ስለነበረ በወቅቱ በተዘጋጀው መጠይቅ መሰረት ከሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን የፍትህ ሚኒስቴር ለአትኩሮት ቡድንና ለቃለ-መጠይቅ የተመቻቸ ጊዜ ሊኖራቸው ባለመቻሉ ሪፖርቱ አለመላኩን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባው ላይ እንደገለፁት ሴክተር መ/ቤቶችን ከመስክ ክትትል አልፎ በሌብሊንግ ቱልስ ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት የስርዓተ-ጾታን ጉዳይ ማካተታቸውን የሚመዝኑ መሆናቸውን የገለፁ ቢሆንም በፍትህ ሚኒስቴር ላይ በመመዘኛው መሰረት የተሰራ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

29. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም ፍትህ ሚኒስቴርን በተመለከተ ያከናወነውን የመስክም ሆነ የሌብሊንግ ቱልስ ሪፖርት የክዋኔ ኦዲቱ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

30. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፍትህ ሚኒስቴርን የየበጀት ዓመት እቅድ ከመገምገም ባሻገር የስርዓተ-ጾታን ጉዳይ ማካተቱን በተመለከተ በመስክም ሆነ በሌቪሊንግ ቱልስ መሰረት ክትትል ባለማድረጉ የሚታዩ ችግሮችን በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዳይወስዱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የሴቶችን ጥቃት የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የአገሪቱ ሕግ አካል ሆነው እንዲፀድቁ መደረጉን በተመለከተ፣**

31. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር  በሴቶች ላይ የሚደርስ ማንኛውንም ዓይነት አድሎ ለማስወገድ የሴቶችን ጥቃት የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች

የአገሪቱ ሕግ አካል ሆነው እንዲፀድቁ ለሚመለከታቸው አካላት ሊቀርብና ጸድቆ የአገሪቱ ሕግ አካል እንዲሆን ሊደረግ ይገባል።

32. ይሁን እንጂ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ህዝቦች የሰብአዊ መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል እንዲፀድቅ ግንቦት 7 ቀን 2001 ዓ.ም ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የላከ ቢሆንም እስካሁን ፀድቆ ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል።

33. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት የአፍሪካ ህዝቦች የሰብአዊ መብት ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል እንዲጸድቅ ቀደም ሲል በ2001 ዓ.ም የማጽደቂያ አዋጁና ማብራሪያ በሚኒስቴር መ/ቤታቸው በኩል እንዲሁም በ2006 ዓ.ም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የቀረበ ቢሆንም ፕሮቶኮሉ ውስጥ የተካተቱ አንዳንድ ሃሳቦች በቅድሚያ የሌሎች ህጎችን መሻሻል የሚጠይቁ በመሆናቸው ልዩ ጥንቃቄ መደረግ ያለበት በመሆኑ እንዲሁም ተጨማሪ ጥናት ተደርጎበት በድጋሚ እንዲቀርብ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ ተሰጥቶበት ጥናቱ በሚኒስቴር መ/ቤታቸውና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል በድጋሚ እየታየና በሂደት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ጥናቱ እንደተጠናቀቀ በድጋሚ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ውሳኔ የሚያገኝ ጉዳይ መሆኑን ገልፀዋል።

**የፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታ ኦዲት እንዲያካሂድ ያደረገውን ክትትል በተመለከተ፣**

34. የሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በፌዴራል ሴክተር መ/ቤቶች እንዲሁም በክልል የሴቶች ጉዳይ የሚመለከታቸው ቢሮዎች የፍትህ ሚኒስቴርን ጨምሮ በሚያከናውኗቸው ተግባራት ውስጥ የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ማካሄዳቸውን የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ በእቅድ በመያዝ ሊከታተል ይገባል።

35. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የፍትህ አካላት ማለትም ለፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ላሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች (ኮልፌ ቀራንዮ፣ ቂርቆስ፣ ልደታና ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተሞች) እንዲሁም ለአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳደር፣ ለኦሮሚያ፣ለሐረሪ፣ ለደቡብ /ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ክልሎች እና ለሲዳማ ዞን ፍትህ ጽ/ቤት ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎች እና ፍትህ ቢሮዎች የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ማካሄዳቸውን የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ በአመታዊ ዕቅድ ውስጥ በማካተት ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል።

36. በሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የሴቶችና ወጣቶች ማካተት ዳይሬክተር በሰጡት ምላሽ በቅድሚያ ትኩረት የሴቶችን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ሦስት (3) ሴክተሮች /ማይክሮ ፋይናንስ፣ ጥቃቅንና አነስተኛና ህብረት ሥራ ተቋማት/ በመምረጥ የፋይናንስና ቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ ስርዓተ-ጾታ ኦዲት እንዲከናወን መደረጉን፣ እንዲሁም ይህ ተሞክሮ ወደ ሌሎች ሴክተሮች ለማስፋት በሚሰጥ ሙያዊ ድጋፍ ግብርና እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ላይ ስርዓተ-ጾታ ኦዲት እየተከናወነ መሆኑን የገለፁ ሲሆን በፍትህ ሚኒስቴር ላይ የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ስለመከናወኑ ሆነ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚደረጉ የሪፖርት ግምገማም ሆነ የምክክር መድረኮች ወቅት ክትትል ስለመደረጉ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃው አልቀረበም፡፡ የፍትህ ሚኒስቴር ደግሞ በ2007 ዓ.ም የስርዓተ ፆታ ኦዲት ለማድረግ የባለሙያ ድጋፍ ሚኒስቴር መ/ቤቱን ጠይቆ እንዳላገኘ በመግለጹ የሰጡትን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

37. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፍትህ ሚኒስቴር ላይ የስርዓተ-ፆታ ኦዲት እንዲከናወን ድጋፍ አለማድረጉ በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን በመገምገም የመፍትሄ አቅጣጫዎችን እንዳያስቀምጥ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

## 2.1.2 የፍትህ ሚኒስቴርን በተመለከተ፣

### ፍትህ ሚኒስቴር ያለውን አደረጃጀት በተመለከተ፣

38. የፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ያሉ ፍትህ ጽ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት የሥርዓተ-ጾታን እኩልነት ለማራመድና ለማስተባበር የሚያስችል አደረጃጀትና ለስራው አስፈላጊ የሆነ በጀት፣ ባለሙያ እና ቢሮ እንዲኖራቸው ሊደረግ ይገባል፡፡

39. በፍትህ ሚኒስቴር የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ማስተባበሪያ ባስጠናው የመሰረታዊ ሂደት ለውጥ ጥናት አደረጃጀት ላይ የሥርዓተ-ጾታ ባለሙያ መኖር እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በስሩ ባሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች የስርዓተ-ጾታን ተግባር የሚያከናውን የስራ ክፍል፣ በጀትና ባለሙያ ያልተመደበ መሆኑ ታውቋል፡፡

40. ስለሁኔታው የፍትህ ሚኒስቴር ኃላፊዎች በሰጡት መልስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ማስተባበሪያ ስርዓተ-ጾታ ባለሙያ ታህሳስ 2007 ዓ.ም በተዘጋጀው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት የተካተተ መሆኑና እስካሁን ግን ተግባራዊ አለመደረጉን ገልፀዋል፡፡

41. በፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ባሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች የስርዓተ ጾታን ጉዳይ እንዲያከናውኑ ለማድረግ እራሱን በቻለ ባለሙያ፣ በጀትና የስራ ክፍል በተሟላ መልኩ ኖሯቸው እንዲሰሩ አለመደረጉ በየጽ/ቤታቸው ፕሮራሞች ላይ የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ በተጠናከረ መልኩ እንዳይከናወን አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

**የፍትህ ሚኒስቴር የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ አመታዊ እቅድ ውስጥ አካቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣**

42. የፍትህ ሚኒስቴር በየአመቱ የሚያዘጋጀው አመታዊ እቅድ የስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ ዕቅዱ ሲዘጋጅ የሥርዓተ ጾታ ጉዳይን ያገናዘበና ያካተተ ሊሆንና በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

43. በናሙና የታዩ በፍትህ ሚኒስቴር ስር ያሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች (ኮልፌ፣ ቂርቆስ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶና ልደታ ክፍለ ከተሞች) የፍትህ ሚኒስቴርን ስትራቴጂክ እቅድ የሚጠቀሙ ሲሆን በየዓመቱ ባሉ እቅዳቸው ላይ በሴቶች ዙሪያ በስልጠና መስጠት፣ በግንዛቤ ማስጨበጥ፣ በቅንጅታዊ አሰራር፣ በመብት ማስከበርና መረጃ አያያዝ ወዘተ… ዙሪያ በሚል የሚከናወኑ ተግባራት በዝርዝር በዕቅዳቸው ውስጥ ተካተው የተቀመጡ ቢሆንም የእቅድ ክንውኑ ሪፖርት ላይ በግልፅ ባለመቀመጣቸው በእቅዱ መሰረት መከናወናቸውን ለማወቅ አልተቻለም፡፡

44. ስለሁኔታው የፍትህ ሚኒስቴር ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በስሩ ስለሚገኙ ፍትህ ጽ/ቤቶች ምንም ዓይነት አስተያየት አለመስጠታቸው ታውቋል፡፡

45. የፍትህ ሚኒስቴር በስሩ የሚገኙ ፍትህ ጽ/ቤቶች ስትራቴጅክ እቅዱ መሰረት በማድረግ በስርዓተ-ጾታ ማካተት ዙሪያ የሚከናወኑ ተግባራት ስለመፈፀማቸው ክትትል ባለማድረጉ ስርዓተ-ጾታን በአግባቡ ተግባራዊ እንዳያደርጉ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

**የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ በፍትህ ሚኒስቴር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተታቸውን በተመለከተ፣**

46. የፍትህ ሚኒስቴር በሚቀርፃቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ውስጥ የስርዐተ-ጾታ ጉዳይ መካተቱን እና ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ መሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

47. የፍትህ ሚኒስቴር በ2004 በጀት ዓመት በተጠሪ ተቋማትና ጽ/ቤቶች የሴቶችና ህፃናት ጉዳዮች መካተታቸውንና መተግበራቸውን ለመከታተልና ለመገምገም በዓመት 4 ጊዜ ግምገማ በማድረግና ክፍተቶችን በመለየት ለማስተካከል በእቅድ የተያዘ ቢሆንም

ተግባራዊ ስለመደረጉ በአፈፃፀም ሪፖርቱ ላይ በግልፅ አልተቀመጠም፡፡ በ2005 እና 2006 በጀት ዓመት በእቅድ ተካቶ ለማከናወን ያልተያዘ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. ስለሁኔታው የፍትህ ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በ2004 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ውስጥ በስራ ሂደቶች፣ በጽ/ቤቶችና በተጠሪ ተቋማት የተደረገ ክትትል በግልፅ ተዘርዝሮ የሚገኝና በ2005 እና 2006 ፍትህ ሚኒስቴር ራሱን በቻለ ግብ በስራ ሂደቶች፣ ጽ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት ክትትልና ድጋፍ እንደተደረገ ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከመውጫ ስብሰባ በኂላ በቀረቡት የ2005 እና 2006 የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች በመመልከት በ2005 ዓ.ም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙ ሁሉም የስራ ሂደቶች የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶችን ጉዳይ በእቅዳቸው ውስጥ አካተው እንዲፈጽሙ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም በእቅዱ መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ ማስረጃው አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም በ2005፣ በ2006 እና በ2007 ዓ.ም በጽ/ቤቶችና በተጠሪ ተቋማትም ክትትልና ድጋፍ ስለመደረጉ ማስረጃው አልቀረበም፡፡

49. የፍትህ ሚኒስቴር ለተጠሪ ተቋማቱም ሆነ በስሩ ላሉ ጽ/ቤቶች የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ ማካተትና መተግበራቸውን በተመለከተ ባቀደው መሰረት ክትትል አለማድረጉ በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ በወቅቱ የማስተካከያና የመፍትሔ እርምጃ እንዳይወስዱ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

### በፍትህ ሚኒስቴር የሚከናወኑ ተግባራት /አመላካቾች በጾታና በእድሜ የተለዩ መሆናቸውን በተመለከተ

50. በፍትህ ሚኒስቴር ስር ያሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች ስርዓተ-ጾታ በተካተቱባቸው በማናቸውም ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አመላካቾች በጾታ የተለዩ ሊሆኑ፣ በሴቶች ላይ በሚደርሱ ጥቃቶች (የሴቶች ግርዛት፣ ወሲባዊ ጥቃቶችና የቤት ውስጥ ጥቃቶች፣ ጠለፋ፣ ዛቻ፣ያለእድሜ ጋብቻ ወዘተ) እና ህገ-ወጥ ዝውውር ላይ የቀረቡ አቤቱታዎችን፣ ክሶችና የተሰጡ ብያኔዎች ዝርዝርና በፈርጅ (በወንጀሉ አይነት) የተደራጀ መረጃ ሊይዙ ይገባል፡፡

51. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ላሉ `ፍትህ ጽ/ቤቶች (ኮልፌ ቀራንዮ፣ ቂርቆስ፣ ልደታና ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተሞች) ከ2007 በጀት ዓመት በአመታዊ እቅዳቸውም ሆነ ሪፖርታቸው ላይ አመላካቾች በጾታም ሆነ በእድሜ የተለዩ መሆናቸውን እና በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በተመለከተ ግን ለተፈፀመባቸው ጥቃት የተሰጡ ብያኔዎችን መረጃዎቹ የማያካትቱ መሆኑ ታውቋል፡፡

52. ስለጉዳዩ የፍትህ ሚኒስቴር መ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሴቶችን የሚመለከቱ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አመላካቾች ሲታቀዱ በጾታ ያልተለዩ የነበረ ሲሆን ነገር ግን ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ሲቀርብ በፆታና በእድሜ የሚለይ ቢሆንም የሚሰጡ ብያኔዎችን በሚያሳይ መልኩ ሪፖርቱ የማይቀርብ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

53. በፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ባሉ የፍትህ ጽ/ቤቶች ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አመላካቾች በጾታ ባለመለየታቸው እንዲሁም በሴቶች ላይ የሚደርሱ ማንኛውም ዓይነት ጥቃቶች ላይ የተሰጠውን ብያኔ/ውሳኔ በሚያሳይ መልኩ አለመቀመጡ የችግሮችን መንስኤ በመረዳት/በማጥናት የመፍትሄ እርምጃዎች እንዳይወሰዱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**በፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ባሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በተመለከተ፣**

54. በፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ባሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች ሴቶች በፍትህ አካላት (በፖሊስ፣ በአቃቢያን ሕግ ወዘተ.....) ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ያሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች፣ ሴቶችን በውሳኔ ሰጪነት ቦታዎች ላይ ያላቸው ተሳትፎ በተመለከተ ካሉት አቃቢያን ሕጎች ውስጥ የሴት አቃቢያን ሕግን ድርሻ 50 ከመቶ ለማድረስ ቢታቀድም አንድ ጊዜ ቅጥር ሲፈፀም ከተቀጠሩት 204 አቃቢያን ሕግ ውስጥ 100 ሴቶች ናቸው ከሚል ነሐሴ 29 ቀን 2007 ዓ.ም ከተፃፈ የውስጥ ማስታወሻ በስተቀር በእቅዱ መሰረት 50 ከመቶ ለመድረሳቸው ማስረጃው አልቀረበም፡፡

56. በፍትህ ሚኒስቴር የሴቶችና ሕፃናት ማስተባበሪያ ኃላፊ በሰጡት መልስ እንደ ፍትህ ሚኒስቴር በዚህ ዙሪያ ብዙ መሰራት ያለበት መሆኑን እንደሚያምኑ አመራርነት ላይ ከተቀመጠው ቦታ ላይ ምን ያህሉ ሴቶች መሆን እንዳለባቸው በግልፅ የተቀመጠ ነገር አለመኖሩን፣ ቅጥርን በተመለከተ 50 በመቶው ለሴት አቃቢያን ሕግ እንደሚሰጥ ሆኖም በልዩ ድጋፍ እርምጃና በአዋጅ 515/99 መሰረት ከተቀጠሩት 204 አቃቢያነ ሕግ ውስጥ 100ዎቹ ሴቶች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

57. በፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ባሉ የፍትህ ጽ/ቤቶች የሴቶችን ተሳትፎ (በፖሊስ፣ በአቃቢያን ሕግ ወዘተ.....) ለማሳደግ የሚያስችል ስርዓት ባለመዘርጋቱ ተጎጂ ሴቶች ሃሳባቸው ግልፅና ነፃ በሆነ መልኩ እንዳይገልፁ እንቅፋት ሊፈጥር ይችላል፡፡

**የሴቶችን መብት በማስጠበቅ ረገድ ቸልተኛ የሆኑ የሕግ አስፈፃሚዎች ተጠያቂ የሚሆኑበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

58. በፍትህ ሚኒስቴርና በስር ያሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች በህግ አስፈፃሚዎች ዘንድ የሴቶችን መብቶች በማስጠበቅ ረገድ ለሚፈፅሙት ቸልተኝነት ተጠያቂ የሚሆኑበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግና በሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተልና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

59. ፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ያሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች የህግ አስፈፃሚዎች የሴቶችን መብት በማስጠበቅ ረገድ ለሚፈፅሙት ቸልተኝነት በአቃቢያን ሕግ አስተዳደር ጉባኤ ደንብ ቁጥር 44/91 አንቀፅ ቁጥር 74(2) መሰረት እንደማንኛውም ወንጀል የሴቶችን ጉዳይ ሆነ ሌሎች ስራዎችን ችላ የሚል ወይም የማይፈፅም ወይም ማንኛውንም የዲሲፕሊን ወይም የሥነ-ምግባር ጉድለት የሚፈጽም አቃቤ ሕግ ስለጥፋቱ በፍትሐ ብሔር ሕግና በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በተወሰነው መሰረት የሚኖርበት ተጠያቂነት ሳይጓደል በዚህ ደንብ መሰረት የሚወሰኑ ቅጣቶች የሚፈፀምባቸው ከመሆኑ ውጭ ሴቶች ከጾታቸው የተነሳ በተፈጸመባቸው ጥቃት ላይ በሚደረግ ቸልተኝነት የተለየ ትኩረት በማድረግ የህግ አስፈፃሚዎች ተጠያቂ የሚሆኑበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

60. ስለሁኔታው የፍትህ ሚኒስቴር ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቸልተኛ የሆኑ የሕግ አስፈፃሚዎችን ተጠያቂ ካደረገባቸው ተግባራት ውስጥ ከ9,000 በላይ አለአግባብ የተዘጉ መዛግብት ውስጥ የሴቶችና ሕፃናት የሚመለከቱ መሆኑ፣ የአንድ የጽ/ቤት ኃላፊ እስከ ስራ ማሳገድ መደረሱን እንደአብነት ሊጠቀስ የሚችል መሆኑን፣ ለሴቶች የተለየ ስርዓት ባይኖርም እንደአጠቃላይ በማንኛውም የወንጀል ዓይነት ጉዳይ ቸል እንደተባለበት አካል እንደሚስተናገዱ ነገር ግን ስራው በአግባቡ እየተሰራ ስለሆነ በተለየ መልኩ ለይቶ መስራት የማያስፈልግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ደግሞ 9000 መዛግብት ሴቶችን የተመለከተ ብቻ አለመሆኑን ነገር ግን የተዘጉ 9000 መዛግብት ድጋሚ ማጣራት ሲደረግ ያለአግባብ ተዘግተው የተገኙ መዛግብት ውስጥ 488ቱ ብቻ አለግባብ የተዘጉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን አለአግባብ ተዘጉ ከተባሉት መዛግብት ውስጥ ከተለዩ 488 መዛግብት ውስጥ ምን ያህሉ ሴቶችና ሕጻናትን የሚመለከቱ መሆናቸውን ለማወቅ አልተቻለም፡፡

61. ሴቶችን የሚመለከቱ አላግባብ የተዘጉ መዛግብት ብዛት 9000 ሆነ 488 ሴቶች እንደሚደርስባቸው የጉዳት መጠን ከሌሎች ክሶች በተለዩ መልኩ ጉዳያቸው

የሚታይበት ሁኔታ አለመኖሩ ለደረሰባቸው ጥቃት አፋጣኝ የሆነ ምላሽ እንዳያገኙ ሊያደርግ የሚችል በመሆኑ ለተለያዩ የስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ችግሮች ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

**የፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ማካሄዱን በተመለከተ፣**

62. የፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታ ኦዲትን በእቅድ ይዞ ሊያከናውን ይገባል፡፡ የተከናወነውንም የኦዲት ሪፖርት ለሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡

63. ይሁን እንጂ የፍትህ ሚኒስቴር ባለፉት አምስት ዓመታት የስርዓተ-ጾታ ኦዲት አለማከናወኑ ታውቋል፡፡

64. ይህንን በተመለከተ የፍትህ ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በ2007 ዓ.ም በእቅድ ይዘው ኦዲት ለማከናወን የሚያግዛቸው ባለሙያ እንዲላክላቸው ከሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በቁጥር 10/03-12/93/3 ጥር 28 2007 ዓ.ም በተፃፈ ቢጠይቁም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ምላሽ ስላላገኙ ኦዲቱን ማከናወን እንዳልቻሉ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልፀዋል፡፡

65. የስርዓተ-ጾታ ኦዲት አለመከናወኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮግራም፣ ፕሮጀክቶችና የተለያዩ ተግባራት ላይ በስርዓተ-ጾታ ዙሪያ ያለውን ጥንካሬና ክፍተት በመለየት ስትራቴጂዎችን በማሻሻል ችግሮች እንዳይፈቱ እንቅፍት ሊፈጥር ይችላል፡፡

**በሴቶች ላይ ስለሚፈፀሙ ጥቃቶች ጥናት መደረጉን በተመለከተ፣**

66. የፍትህ ሚኒስቴር በሴቶች ላይ ስለሚፈፀሙ ጥቃቶች ጥናት ማድረግ አለበት፡፡ በጥናቱም መሰረት ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡

67. ይሁን እንጂ ፍትህ ሚኒስቴር በስትራቴጂክ ዘመኑ ከ2003-07 ዓ.ም ድረስ በሴቶች ላይ ስለሚፈፅሙ ጥቃቶች በተመለከተ በእያንዳንዱ ዓመት 12 የክፍተት ጥናቶችን ለማድረግ አቅዶ አንድ ጥናት ብቻ ያከናወነ መሆኑ ታውቋል፡፡

68. በፍትህ ሚኒስቴር የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ማስተባበሪያ ኃላፊ በሰጡት ምላሽ ጥናቶቹ ያልተሰሩበት ምክንያት ከዚህ በፊት ተቋሙ ስርዓተ-ጾታን ባካተተ መልኩ እየሰራ የነበረ ባለመሆኑ፣ በመ/ቤቱ ያሉ ሁሉም ክፍሎች የመያዝ ልምድ ያልነበረ በመሆኑ፣ በክፍሉ ያለ የሰው ኃይል አነስተኛ መሆን፣ ክፍሉ እንደራሱ ስራ ቆጥሮ እንዲሰራ ባለመደረጉ፣ ደራሽ (ድንገት) የሚመጡ ስራዎች የሚበዙ በመሆናቸው ጥናቱ ሊሰራ አለመቻሉ ባጠቃላይ የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ በተቋሙ ብዙ የሚቀረው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

69. በሴቶች ጥቃት ዙሪያ በየወቅቱ ጥናት አለማከናወን ሴቶች በጥቃት አማካኝነት የሚደርስባቸውን ስነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በወቅቱ እንዳይቀርፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 2.2. የሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከፍትህ ሚኒስቴር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ከፍትህ ጋር በተያያዘ የሥርዓት ፆታ ጉዳይ ተካቶ ተግባራዊ ለማድረግ በቅንጅት የሚሰሩበት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲሁም መደበኛ የመወያያ መድረክ የዘረጉና ተግባራዊ ያደረጉ መሆኑን በተመለከተ፣

**በሴቶች ዙሪያ በሚወጡ ሕጎች ላይ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ መስጠቱን በተመለከተ፣**

70. የፍትህ ሚኒስቴር በየጊዜው ከሥርዓተ ጾታ ጋር በተያያዙ የሚወጡ ሕጎችን፣ ደንቦችንና አለምአቀፍ ስምምነቶችን አስመልክቶ እቅድ ውስጥ በማካተት ከሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በህትመትና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች (በሬድዮ፣ በቴሌቪዝን፣ በጋዜጣ፣ በመፅሄት፣ በበራሪ ወረቀቶች፣ በድረ-ገፅ በመሳሰሉት) ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ሊሰራ ይገባል፡፡

71. የፍትህ ሚኒስቴርና በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ በስሩ ያሉ አራት ፍትህ ጽ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትና የክልል/የከተማ መስተዳደር ፍትህ ቢሮዎች ከሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት (በሴቶች ዙሪያ ከሚሰሩ ተቋማት) ጋር በመተባበር በየጊዜው የሚወጡ ሕጎችን አስመልክቶ የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን በመጠቀም ህጎቹን በተመለከተ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ያልሰሩ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ሁለቱም ሚኒስቴር መ/ቤቶች ድህረ ገጽ ያላቸው ቢሆንም እነዚህ ህጎች ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ በድህረ ገጾቻቸው ላይ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተጫኑ መሆኑ ታውቋል፡፡

72. በሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የሴቶችና ወጣቶች ንቅናቄና ተሳትፎ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሰጡት መልስ መ/ቤቱ በኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ በፋና ብሮድካስቲንግ አማካኝነት ከዩኒሴፍ ባገኘው እርዳታ መሰረት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በቀጥታ ለህብረተሰቡ የሚያስተላልፍ መሆኑን፣ ለፍትህ አካላትም የሴቶችን ጉዳይ በተሻለ መልኩ እንዲያከናውኑ አቅም የመገንባት ስራዎችን የሚሰሩ መሆኑን ቢገልፁም ማስረጃው ለኦዲቱ አልቀረበም፡፡፡

73. በፍትህ ሚኒስቴር የሴቶችና ሕፃናት ማስተባበሪያ ኃላፊ ለተጠሪ ተቋማት ማለትም ለሰነዶች ማረጋገጫ፣ህግና ፍትህ ምርምርና ለወሳኝ ኩነቶች የስራ ባህሪያቸው ግንዛቤ ስጡ ለማለት አመቺ ባለመሆኑ ድጋፍ የማያስፈልጋቸው መሆኑን፣ ቅ/ጽ/ቤቶችን በተመለከተ በየክ/ከተማቸው ለሚኖረው ነዋሪ በሴቶች ዙሪያ ስልጠና ሊሰጡ ያሰቡትን ርዕሰ ጉዳይ ባሳወቁት መሰረት አጋዥ ማቴሪያሎች የተላካለቸው መሆኑን ቢገልፁም መላካቸውን የሚገልፅ ማስረጃ ለኦዲቱ አለመቅረቡ እንዲሁም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫው ላይ በሰጡት መልስ  በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ማለትም በሬዲዮ የንቃት ህግ ግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባር ያከናወነና የኦዲት ቡድኑ ማስረጃውን ከመ/ቤታቸው ከህግ ጥናት፣ ማርቀቅና ማስረጽ ዳይሬክቶሬት እንዲያገኝ ያመቻቹ መሆኑን ቢገልፁም ማስረጃው ለኦዲቱ አለመቅረቡ ታውቋል፡፡ ህጎቹ በድህረ ገጾቻቸው ላይ ለምን እንዳልተቀመጡ ግን የሁለቱም ሚኒስቴር መ/ቤት ኃላፊዎች የሰጡት ምላሽ የለም፡፡

74. ሴቶችን በሚመለከት በየጊዜው የሚወጡ ሕጎችን በተመለከተ ለህብረተሰቡ በየጊዜው ግንዛቤ አለመሰጠቱ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዳይቀንሱ፣ ስለ ሴቶች በማህበረሰቡ ላይ ያለው በጎ ያልሆነ አመለካከት እንዳይለወጥና ሴቶች መብቶቻቸውን ለይተው በማወቅ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች የሚደረግላቸውን ድጋፍና እገዛ በተመለከተ፣**

75. በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ጉዳት የደረሰባቸውን ሴቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍና እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

76. የፍትህ ሚኒስቴር በአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅዱ በሴቶች ላይ የሚፈፀም ጥቃት ጉዳት የደረሰባቸውን ሴቶች እንክብካቤ ማዕከልን በአራት ሆስፒታሎች ለማስገንባት እቅድ ቢይዝም እስከ 2007 በጀት ዓመት ድረስ አንድ ማለትም በጋንዲ ሆስፒታል የሚገኘውን ማዕከል ብቻ የተገነባ መሆኑ ታውቋል፡፡

77. በፍትህ ሚኒስቴር የሴቶችና ሕፃናት ማስተባበሪያ ኃላፊ በሰጡት መልስ በፍትህ ሚኒስቴር ስትራቴጂክ እቅድ ውስጥ ሁለት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ለመገንባት አቅዶ እንደነበርና የአንዱ ቦታ መከናወኑን ነገር ግን ሌላኛውን ማከናወን ያልተቻለው በጊዜው አጋጥሞ በነበረው የቦታ ችግርና የብሔራዊ አስተባባሪው አካል (ፍትህ ሚኒስቴርና እና ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይን ጨምሮ 16 የፌዴራል ሴክተር መ/ቤቶችና በሴቶች ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማት) ተጠናክረው ባለመስራታቸው ችግሩ

መከሰቱን የገለፁ ሲሆን ስለ ቀሪዎቹ ሁለት ማእከላት ግን ምንም አይነት አስተያየት አልሰጡም፡፡

78. በሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የሴቶችና ወጣቶች ንቅናቄ ተሳትፎ ማስፋፊያ ዳይሬክተር እንደገለፁት ከክፍላቸውና ከሕግ አገልግሎት ክፍል አንድ አንድ ባለሙያ በመመደብ አስተባባሪ ኮሚቴው በሚያከናወናቸው ተግባራት የክትትልና የጥናት ስራ እንዲሳተፉ እያደረገ መሆኑን እንዲሁም በgender joint program በየዓመቱ ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር በመደራደር በጀት በማስያዝ ቀጥታ ለጤና ጥበቃ እንዲላክ በማድረግ የማስተባበር ስራውን እንደሚያከናውኑ ቢገልፁም ማስረጃው ለኦዲቱ አልቀረበም፡፡

79. ተጠቂ የሆኑ ሴቶችን እንክብካቤ ሊያገኙ የሚችሉባቸው ማዕከላት በታቀደው መሰረት ባለመገንባታቸው/ተደራሽነታቸው ባለመጨመሩ ለደረሰባቸው አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ችግሮች በወቅቱ መፍትሄ እንዳያገኙ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

80. የፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ ለማካተት የዘረጋው ሥርዓት ውጤታማና ብቃት ባለው መልኩ እየተተገበረ መሆኑን እንዲሁም የተዘረጋውን ሥርዓት ለመተግበር የሚካሄደው ቅንጅታዊ አሰራር ውጤታማ መሆኑን ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

81. **የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርን በተመለከተ፣**

- ❖ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታን በሚመለከት ያዘጋጃቸውን መመሪያዎች ለፍትህ ሚኒስቴር እና የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎች ለሚመለከታቸው ሁሉ ስለመሰራጨቱም ሆነ ሥልጠና ስለመሰጠቱ መረጃ አለመቅረቡ፣
- ❖ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ፍትህ ሚኒስቴር የሴቶችን ጉዳይ በማካተት ዙሪያ ያለበትን ደረጃ ለማወቅ የመስክ ክትትል በማድረግ በታዩ ችግሮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ያላሳወቀና ያልተከታተለ መሆኑ፣
- ❖ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በፌዴራል ሴክተር መ/ቤቶች እንዲሁም በክልል የሴቶች ጉዳይ የሚመለከታቸው ቢሮዎች እና የፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ማካሄዳቸውን የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ያልተከታተለ መሆኑ፣
- ❖ የሥርዓተ ጾታ ኦዲት በፍትህ ሚኒስቴር ለማከናወን ድጋፍ አለማድረጉ፣

82. **የፍትህ ሚኒስቴርን በተመለከተ፣**

- ❖ ፍትህ ሚኒስቴርም ሆነ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ በስሩ ያሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች የስርዓተ-ጾታን ለማከናወን ተብሎ የተዘጋጀ በጀት፣ ቢሮና ባለሙያ የሌላቸው መሆኑ፣
- ❖ በፍትህ ሚኒስቴር ሥር ባሉ በናሙና በታዩ ፍትህ ጽ/ቤቶች (ኮልፌ፣ ቂርቆስ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶና ልደታ ክፍለ ከተሞች) የፍትህ ሚኒስቴርን ስትራቴጂክ እቅድ ተጠቅመው በየዓመቱ ባለው እቅድ ላይ በሴቶች ዙሪያ ስልጠና መስጠት፣ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ ቅንጅታዊ አሰራር፣ መብት ማስከበርና መረጃ አያያዝ ወዘተ… ዙሪያ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ያልታየና ዕቅዱም ያልተገመገመ መሆኑ፣
- ❖ የፍትህ ሚኒስቴር በ2004 ዓ.ም በተጠሪ ተቋማትና ፍትህ ጽ/ቤቶች የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ትኩረት ሰጥተው ማካተታቸውንና መተግበራቸውን በዓመት 4 ጊዜ በመገምገም ክፍተቶችን በመለየት ለማስተካከል በእቅድ ተይዞ አለማከናወኑ፣ እንዲሁም በቀጣዩ 2005፣ 2006 እና 2007 በጀት ዓመት እቅድ ክንውን ሪፖርት ላይ የሌለ መሆኑ፣

- ❖ በፍትህ ሚኒስቴር ስር የሚገኙ በናሙና የታዩ ፍትህ ጽ/ቤቶች እና ፍትህ ቢሮዎች እቅዳቸውም ሆነ በሪፖርታቸው አመላካቾች በጾታና በዕድሜ ያልተለዩ እና በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በተመለከተ የተሰጡ ብያኔዎችን ሚያሳይ መልኩ የተደራጀ መረጃ የሌለ መሆኑ፣
- ❖ በፍትህ ሚኒስቴርና በናሙና በታዩ በስሩ ባሉ ጽ/ቤቶች ሴቶች በውሳኔ ሰጪነት ቦታዎች ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ ሥርዓት አለመዘርጋታቸው፣
- ❖ በፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ባሉ የፍትህ ጽ/ቤቶች፣ በናሙና በታዩ የፌደራልና የክልል ፍትህ ቢሮዎች ሴቶች እንደደረሰባቸው የጉዳት መጠን የማያስተናግዱና የሴቶችን ጉዳይ ችላ የሚሉ የህግ አስፈፃሚዎች ተጠያቂ የሚሆኑበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ የሚያደርግ ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- ❖ ፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታ ኦዲት በማከናወን ሪፖርቱን ለሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የማይልክ መሆኑ፣
- ❖ ፍትህ ሚኒስቴር በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በተመለከተ በስትራቴጂክ ዕቅዱ በየአመቱ 12 የክፍተት ጥናት ለማድረግ አቅዶ 1 ብቻ ያከናወነ መሆኑ፣

## የሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍትህ ሚኒስቴርና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰሩበት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት የዘረጉና ተግባራዊ ያደረጉ መሆኑን በተመለከተ፣

- ❖ የፍትህ ሚኒስቴር ከሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴና ከሌሎች ከባለድርሻ አካላት (በሴቶች ዙሪያ ከሚሰሩ) ጋር በየጊዜው የሚወጡ ሕጎችን የየሚኒስቴር መ/ቤቱን የመረጃ መረብን በመጠቀም (በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች) ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን ያልሰጡ መሆኑ፣
- ❖ የፍትህ ሚኒስቴር በአምስት ዓመት ስትራቴጂ እቅዱ በሴቶች ላይ በሚፈፀም ጥቃት ጉዳት ለደረሰባቸው ሴቶች የእንክብካቤ ማዕከል በአራት ሆስፒታሎች ለማስገንባት ቢያቅድም አንድ ማዕከል ብቻ የገነባ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

83. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

84. የስርዓተ-ፆታን ጉዳይ በፍትህ ሚኒስቴር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ማካተት የሚያስችል ብቃት ያለው ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

85. **የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርን በተመለከተ፣**

- የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ሥርዓተ ጾታን በሚመለከት ያዘጋጃቸውን መመሪያዎች ለፍትህ ሚኒስቴር እና ከፌዴራል እስከ ክልል ላሉ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎች ሊያሰራጭ እና ባሰራጫቸው መመሪያዎችም ላይ ስልጠና በመስጠት ተግባራዊ መደረጋቸውን ዕቅድና ፕሮግራም በማውጣት ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የፍትህ ሚኒስቴር በስርዓተ ጾታ ማካተቻ ጋይድላይኑ መሰረት የሴቶችን ጉዳይ በማካተት ዙሪያ ያሉበትን ደረጃ ለማወቅ የመስክ ክትትል በማድረግ በታዩ ችግሮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ሊያሳውቅ፣ ድጋፍና ክትትልም ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የፌዴራል ሴክተር መ/ቤቶች እንዲሁም በክልል የሴቶች ጉዳይ የሚመለከታቸው ቢሮዎች እና የፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ማካሄዳቸውን የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊከታተልና ሊደግፍ ይገባል፣

86. **የፍትህ ሚኒስቴርን በተመለከተ፣**

- የፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ያሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች የሥርዓተ-ጾታን እኩልነት ለማራመድና ለማስተባበር እንዲያስችል በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (BPR) ጥናት በተቀመጠው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሰረት እራሱን የቻለ የስራ ክፍል፣ በጀትና ባለሙያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- ፍትህ ሚኒስቴር እና በሥሩ ያሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች በስትራቴጂክ እቅዳቸው መሰረት በየዓመቱ የሚያዘጋጁትን አመታዊ እቅድ በየጊዜው በመገምገም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያሳውቁበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፣


- ❖ ፍትህ ሚኒስቴር በስሩ ባሉ ፍትህ ጽ/ቤቶችና በተጠሪ ተቋማቱ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቶት መካተቱንና መተግበሩን በየአመቱ በእቅድ ይዞ በመገምገም ክፍተቶችን በመለየት ማስተካከልና ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፣
- ❖ በፍትህ ሚኒስቴር ስር የሚገኙ ፍትህ ጽ/ቤቶች እና ፍትህ ቢሮዎች በእቅዳቸው እና በእቅድ አፈጻጸም ሪፖርታቸው አመላካቾች በጾታና በዕድሜ እንዲቀመጡ እና በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በተመለከተ የተሰጡ ብያኔዎችን በሚያሳይ መልክ የተደራጀ መረጃ እንዲያዝ መደረግ ይኖርበታል፣
- ❖ በፍትህ ሚኒስቴርና በስሩ ባሉ ፍትህ ጽ/ቤቶች በውሳኔ ሰጭነት ቦታዎች ላይ (በዳኝነት፣ አቃቢ ህግ…. ወዘተ) የሴቶችን ቁጥር ከወንዶች እኩል እንዲሆን ልዩ የሆነ የድጋፍ ስራ ሊሰራ ይገባል።
- ❖ የፍትህ ሚኒስቴር የሴቶችን ጉዳይ ችላ በሚሉ የህግ አስፈጻሚ አካላት ላይ የተለየ ተጠያቂነት ስርዓትና የቅጣት አፈጻጸም ስርዓት በመዘርጋት ክፍተት ከተገኘባቸው መዛግብት ውስጥ ሴቶችን በሚመለከት የተያዙ መዛግብት በአግባቡ ተጣርተው ተገቢውን ውሳኔ እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል።
- ❖ ፍትህ ሚኒስቴር የስርዓተ-ጾታ ኦዲት በማከናወን ሪፖርቱን ለሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲላክ ሊያደርግ ይገባል፣
- ❖ ፍትህ ሚኒስቴር በስትራቴጂክ ዕቅዱ መሰረት በየበጀት ዓመቱ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ የክፍተት ጥናቶችን በማከናወን እና ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ ጥቃቶች የሚቀንሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባዋል።

87. **የሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰሩበት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት የዘረጉና ተግባራዊ ያደረጉ መሆኑን በተመለከተ፣**

- ❖ የፍትህ ሚኒስቴር ከሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርና ከሌሎች ከባለድርሻ አካላት (በሴቶች ዙሪያ ከሚሰሩ) ጋር በመተባበር በየጊዜው የሚወጡ ሕጎችን በመረጃ መረቦቻቸው ላይ በማስቀመጥ (በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች) የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ዝግጅቶችን ሊሰጡና መረጃ ፈላጊዎች በቀላሉ እንዲገኙ ሁኔታዎቹን ሊያመቻቹ ይገባል።
- ❖ የፍትህ ሚኒስቴር በቀጣይ አምስት ዓመት ስትራቴጂ እቅዱ በሴቶች ላይ በሚፈፀም ጥቃት ጉዳት የሚደረሰባቸው ሴቶች ተገቢ እንክብካቤ እንዲያገኙ ከሁሉም ክልሎች ጋር በመተባበር ያለውን የሴቶች ቁጥር ያገናዘበና ለአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ የሚሆኑ ማዕከላትን መገንባት ይኖርበታል።

88. በመጨረሻም የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የፍትህ ሚኒስቴር፣ በአዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ለታዩት ድሬዳዋ መስተዳድር፣ ሐረሪ እና ደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ ክልሎች ለሚገኙ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎች እና የፍትህ ቢሮዎች እንዲሁም ለአዲስ አበባ ከተማ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ እና ፍትህ ቢሮ እና ኮልፌ ቀራንዮ፣ ልደታ፣ ቂርቆስና ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የፍትህ ጽ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1፡ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር መዋቅር



# አባሪ 2: የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች<br>/Audit Issues/ | የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች<br>/Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| 1. የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ በፍትህ ዘርፉ በሚዘጋጁ እቅድና ፕሮግራም ውስጥ መካተቱን፣ ለአፈፃፀምና ክትትል የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፡፡<br>1.1 የሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር የፍትህ ሚ/ር የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ ስለማካተቱ በየበጀት ዓመቱ ክትትል የሚያደርበት ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣ | 1. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም የሚያስችል በወጣው አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት አደረጃጀት እንዲኖረው መደረግ አለበት፡፡ |
| | 2. በየደረጃው ያሉ የሴቶችን ጉዳይ ለማስፈፀም የተቋቋሙ አካላት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡<br>በሚያዘጋጁትም ስትራቴጂክ እቅድ ውስጥ የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ መካተቱን አፈፃፀምና ክትትል ስለሚያከናውኑበት ዘዴ በግልጽ ሊያስቀምጡ ይገባል፡፡ |
| | 3. የሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር በየደረጃው ባሉ የፍትህ አካላት ለሚያደርገው የመስክ ክትትል በዓመታዊ እቅድ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | 4. የሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር በየደረጃው ባሉ የፍትህ አካላት በመስክ ክትትል ወቅት በታዩ ችግሮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ሊያሳውቅና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 5. የሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር በየደረጃው ካሉ የፍትህ አካላት የተላከውን የስርዓተ-ጾታ ማካተት እቅድና ክንውን በመገምገም ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 6. የሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር የስርዓተ-ጾታን በሚመለከት ባዘጋጃቸው መመሪያዎች (ብሔራዊ የስርዓተ-ጾታ ማካተቻ ጋይድላይን ፣ የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ማንዋል..) ላይ ለፍትህ ሚ/ር፣ ለክልል የሴቶች ጉዳይና የፍትህ ቢሮዎች ስልጠና ሊሰጥና ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 7. የሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር የስርዓተ-ጾታ በሚመለከት ያዘጋጃቸው መመሪያዎች የሴክተር መ/ቤቶች ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊከታተልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 8. የሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር በሴቶች ዙሪያ የሚወጡ ህጎችና አገሪቱ የተቀበለቻቸው ዓለም ዓቀፍና አህጉር ዓቀፍ ስምምነቶች ላይ ከፌዴራል እስከ ክልል ባሉ የፍትህ ቢሮዎችና የሴቶች ጉዳይ ቢሮዎች ግንዛቤ የሚያገኙበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 9. የሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት በሚያከናውኗቸው ተግባራት ውስጥ የስርዓተ-ጾታ ኦዲት ማካሄዳቸውን በእቅድ በመያዝ ሊከታተል ይገባል፡፡ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ | የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| | 10. የሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር በሴቶች ላይ የሚደርስ ማንኛውንም ዓይነት አድሎ ለማስወገድና ለሴቶች ጥቃት ፍትሕ ቀጥተኛ አግባብነት ያላቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የአገሪቱ ሕግ አካል ሆነው እንዲፀድቁ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |
| 1.2 የፍትህ ሚ/ር የስርዓተ-ጾታ ማካተት የእቅድ አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣ | 11. በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት የሥርዓተ-ጾታን እኩልነት ለማራመድና ለማስተባበር ለስራው አስፈላጊ የሆነ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 12. በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት በየአመቱ የሚያዘጋጁት አመታዊ እቅድ የስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 13. በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት ሴቶች በፍትህ አካላት ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ ስርዓት ዘርተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል |
| | 14. በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት በስትራቴጂክ እቅዱ መሰረት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ውስጥ የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ እንዲካተት በማድረግ አመታዊ እቅድና የእቅድ ክንውን ሪፖርት ለሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር መላክ አለባቸው፡፡ |
| | 15. በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት በሚቀርጿቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን የስርዐተ-ጾታ ጉዳይን ሊያካትቱ ይገባል፡፡ |
| | 16. በየደረጃው ባሉ የፍትህ አካላት ስርዓተ-ጾታ በተካተቱባቸው በማናቸውም ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አመላካቾች በጾታ የተለዩ ሊሆኑ ይገባል፡፡ |
| | 17. በየደረጃው ባሉ የፍትህ አካላት ሴቶች ከፍትህ ስርዓቱ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 18. በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት በሚያዘጋጁት አመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ በፍትህ ዘርፍ የፕሮግራምና ፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ በስርዓተ-ጾታ ዙሪያ የታዩ ክፍተቶች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ማካተት አለባቸው፡፡ |
| | 19. በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት በህግ አስፈፃሚዎች ዘንድ የሴቶች መብቶችን በማስጠበቅ ረገድ ለሚፈፅሙት ቸልተኝነት የተጠያቂነት ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | 20. በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት ፈቃድ ባላቸው ጠበቆች በየዓመቱ የሚሰጠውን የ50 ሰዓት ነፃ የሕግ አገልግሎት ድጋፍ ውስጥ ሴቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ | የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| | ይገባል፡ |
| | 21. በየደረጃው ባሉ የፍትህ አካላት ሴቶች ፈቃድ ባላቸው ጠበቆች የሚሰጠውን 50 ሰዓት ነፃ የሕግ አገልግሎት ድጋፍ ተጠቃሚ ስለመሆናቸው በየዓመቱ ለሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል |
| | 22. በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት የስርዓተ-ጾታ ኦዲትን በእቅድ ይዞ በማከናወን ሪፖርቱን ለሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር መላክ አለባቸው፡፡ |
| | 23. በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት በሴቶች ላይ ስለሚፈፀሙ ጥቃቶች ጥናት ማድረግ አለባቸው፡፡ በጥናቱም መሰረት ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው |
| 3. የሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከፍትህ ሚ/ር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ከፍትህ ጋር በተያያዘ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ተካቶ ተግባራዊ ለማድረግ በቅንጅት የሚሰሩበት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲሁም መደበኛ የመወያያ መድረክ የዘረጉና ተግባራዊ ያደረጉ መሆኑን መገምገም፤ | 24. የሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር ከፍትህ ሚ/ርና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት (ከክልል ሴቶች ጉዳይ ቢሮዎች፣ ከፌዴራልና ክልል ፍትህ አካላት፣ ከአገር አቀፍና አለም አቀፍ የልማት አጋሮች) ጋር የመግባቢያ ሰነድ (MoU) ሊፈራረም እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 25. የሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት በየበጀት ዓመቱ የስርዓተ-ጾታ ጉዳይን በእቅዳቸው በማካተት የእቅድ ክንውን ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 26. የሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር በየደረጃው ካሉ የፍትህ አካላትና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ከእቅድ እስከ ውጤት በመናበብና በመደጋገፍ የሴቶችንና የወጣቶችን በሁሉም ዘርፍ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን በሚመለከት የተነሱ ችግሮች መፍትሄ የሚያገኙበት ስርዓት ለማረጋገጥ በየሩብ ዓመቱ የመወያያ መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 27. በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት በየጊዜው የሚወጡ ሕጎችን አስመልክቶ እቅድ ውስጥ በማካተት ከሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በህትመትና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች (በሬድዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣ፣ በመፅሄት ፣ በበራሪ ወረቀቶች፣ በድረ-ገፅ በመሳሰሉት) ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 28. በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት በሴቶች ላይ በሚደርሱ ጥቃቶች (የሴቶች ግርዛት ወሲባዊና የቤት ውስጥ ጥቃቶች ወዘተ) እና ህገ-ወጥ ዝውውር ላይ የቀረቡ አቤቱታዎችን፣ ክሶችና የተሰጡ ብያኔዎች ዝርዝርና በፈርጅ የተደራጀ መረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | 29. በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ጉዳት የደረሰባቸውን ሴቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍና እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ |

## አባሪ 3: በናሙና የታዩ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎችና የፍትህ ቢሮዎች

| ተ.ቁ | ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው የሴ/ህ/ወ/ጉ/ቢሮዎች | ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው የፍትህ ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች |
|---|---|---|
| 1 | የድሬዳዋ መስተዳድር ሴ/ህ/ወ/ጉ/ቢሮ | የድሬዳዋ መስተዳድር ፍትህ ቢሮ |
| 2 | የሐረሪ ክልል ሴ/ህ/ወ/ጉ/ቢሮ | የሐረሪ ክልል ፍትህና ፀጥታ ጉዳዮች |
| 3 | የደ/ብ/ብ/ሕ/ ክልል ሴ/ህ/ወ/ጉ/ቢሮ | የደ/ብ/ብ/ሕ/ ክልል ፍትህ ቢሮ<br>ለሲዳማ ዞን ፍትህ ጽ/ቤት |
| 4 | የኦሮሚያ ክልል ሴ/ህ/ወ/ጉ/ቢሮ | የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ |
| 5 | የአ.አ ሴ/ህ/ወ/ጉ/ቢሮ | የአ.አ ፍትህ ቢሮ |
| 6 | ለሴ/ህ/ወ/ጉ/ሚ/ር | ለፍትህ ሚ/ርና በስሩ ላሉ ፍ/ጽ/ቤቶች<br>1. ለልደታ<br>2. ለኮልፌ<br>3. ለቂርቆስ<br>4. ለንፋስ ስልክ ላፍቶ |